በፓሪስ ከተማ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ህዳር 23 ቀን 2004 ዓ.ም. የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ቦንድ ግዢ አከናወኑ፡፡ ቀደም ሲል ይህን ሥራ ለማስተባበር የተቋቋመው በፈረንሣይ የዳያስፖራ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ከኤምባሲው ጋር በጋራ ባዘጋጁት በዚህ ዝግጅት ከ100 በላይ ኢትዮጵያውያን የታደሙ ሲሆን በዕለቱ በተከናወነ ሽያጭ 14,080 ዩሮ በእጅ ዩሮ 3,800.00 ቃል የተገባ ሲሆን፣ 120 በስጦታ በጠቅላላው ዩሮ 18,050.00 ሽያጭ ተከናውኗል፡፡ ቀደም ሲል 2,500.00 ዩሮ በካሽ፣ 900.00 በስጦታ በጠቅላላው ዩሮ 21,450.00 ወይም 543.757 ብር ሽያጭ ተከናውኗል፡፡

በዝግጅቱ ላይ በፈረንሣይ የኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ባደረጉት ንግግር ዜጐች በአገራቸው ልማት እንዲሳተፉ መንግስት ሁኔታዎችን ያመቻቸ መሆኑን በመግለጽ ለዘመናት ለትውልዶች ጥቅም ላይ ያልዋለን የተፈጥሮ ሃብት ጥቅም ላይ ለማዋል መንግስት ቁርጠኛ እርምጃ መውሰዱን አብራርተዋል፡፡ አያይዘው ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ይህን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የዚህ ታሪክ አካል እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ምክር ቤቱ ቀጣይ ፕሮግራሞችን በፓሪስና በሌሎች ከተሞች ለማዘጋጀት መርሐ ግብር አዘጋጅቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኤምባሲ
ፓሪስ

| | |
|---|---|
| Filename: | Ethiopian Embassy Paris |
| Directory: | C:\Documents and Settings\emb\Desktop |
| Template: | C:\Documents and Settings\emb\Application Data\Microsoft\Templates\Normal.dot |
| Title: | |
| Subject: | |
| Author: | praivet |
| Keywords: | |
| Comments: | |
| Creation Date: | 09/12/2011 6:02 PM |
| Change Number: | 1 |
| Last Saved On: | |
| Last Saved By: | |
| Total Editing Time: | 0 Minutes |
| Last Printed On: | 09/12/2011 6:03 PM |

As of Last Complete Printing

| | |
|---|---|
| Number of Pages: | 1 |
| Number of Words: | 114 (approx.) |
| Number of Characters: | 651 (approx.) |